Dream Success Academy
ድሪም ሰክሰስ አካዳሚ
P.O. Box 50010 Tel: ዐ118356935/ዐ118356936 Email Dream

ስም _____ ክፍል **6** የት.ት አይነት: አ/ሳይንስ
ቀን _____**2016** አ.ም መለማመጃ ጥያቄ

I. <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛ መልስ የያዘዉን ፊደል በመምረጥ መልሱ:</u>

___1. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ ደምን የሚረጨዉ የሰዉነታችን አካል ክፍል የቱ ነዉ?
ሀ. ሰርን ለ. ሳንባ ሐ. ልብ መ. የአፍ ወና

____2. ኦክስጂንን ከሳንባ ተቀብለዉ በመሸከም ለመላ የሰዉነታችን ህዋሶች የሚያደርሱ የደም ህዋስ አይነት የሆነዉ የቱ ነዉ?
ሀ. ፕሌትልቶች ለ. ቀይ የደም ህዋስ ሐ. ደም መልስ መ. ነጭ የደም ህዋስ

_____3. ከሚከተሉት ዉስጥ ደምን ከልብ ወደ ተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች የሚያሰራጨዉ የደም ሥር አይነት----------ይባላል።
ሀ. ደም መልስ ለ. ቀጫኙን የደም ስር ሐ. ደም ቅዳ መ. ልብ

____4. አየር እና ምግብ በጋራ የሚተላለፍባቸዉ የሰዉነታችን አካል ክፍል የሆነዉ የቱ ነዉ?
ሀ. ተገንጣይ ባላትንባ ለ. ድህረ-አፍ ሐ. አፍንጫ መ. የአየር ከረጢት

___5. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ አንዱ የታችኛዉ የሥርዓተ-ትንፈሳ ክፍል ነዉ።
ሀ. ድህረ-አፍ ለ. ሰርን ሐ. ሰርን መ. ዐብይ ትንባ

____6. ከሚከተሉት ዉስጥ አንዱ በወንዶች ላይ የሚታይ አካላዊ ለዉጥ ነዉ።
ሀ. የዳሌ መስፋት ለ. የወር አበባ ማየት
ሐ. የድምፅ መጎርነን መ. የጡት ማደግ

____7. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ ደም ለማርጋት የሚጠቅም የደም ህዋስ አይነት የሆነዉ የቱ ነዉ?
ሀ. ቀጫጭን የደም ስሮች ለ. ቀይ የደም ሕዋስ ሐ. ነጭ የደም ህዋስ መ. ፕሌትሌቶች

__8. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ አንዱ የዋህደ-ዘር ድብልቅ ምሳሌ ነዉ።
ሀ. ደም ለ. አየር ሐ. ወተት መ. የዘይትና የዉሃ ድብልቅ

__9. አየርን ወደ ሰዉነታችን ዉስጥ የምናስገባበት ሂደት ----------ይባላል።
ሀ. የልብ ምት ለ. ምጋት ሐ. ሳንባ መ. ኢ-ምጋት

_10. ከአየር ጋር የሚገቡትን ቆሻሻዎችን እና ጀርሞችን በማጣራት ንጹህ አየር የሚሰጠን የአካላችን ክፍል የሆነዉ የቱ ነዉ?
ሀ. ልብ ለ. አፍ ሐ. ሰርን መ. እንጥል

___11. ከሚከተሉት ዉስጥ ስለ ልይ-ዘር ድብልቅ ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?
ሀ. የድብልቁን ምንዝሮች በአይን መለየት አይቻልም
ለ. የድብልቁ ምንዝሮች ወጥና ተመሳሳይ ነዉ።
ሐ. የድብልቁ ይዘት ወጥና ተመሳሳይ አይደለም።
መ. የጨዉ ሙሙት የልይ-ዘር ምሳሌ ነዉ።

___12. አየርን ከሰዉነታችን ዉስጥ የምናስወጣበት ሂደት ----------ይባላል።
ሀ. ደም ቀዳ ለ. ምጋት ሐ. ደም መልስ መ. ኢ-ምጋት

___13. የልብ ትርታን ማዳመጫ መሳሪያ ምን ይባላል?
ሀ. ስቴቶስኮፕ ለ. ድግሪ ሐ. ካርታ መ. ኬክሮስ

____14. በሰዉነታችን ዉስጥ የሚገኝ የደምስር አይነት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?
ሀ. ደም መልስ ለ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ሐ. ደም ቅዳ መ. ቀጫጭን ደም ሥሮች

_____15. በኦክስጅን የበለፀገ ደም የሚተላለፍባቸዉ የልብ ቧንቧ አይነቶች--------እና -------ናቸዉ።

ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ እና ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ለ. ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ እና ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

ሐ. ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ እና ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ

መ. ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ እና ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

____16. ከሚከተሉት አማራጮች ዉስጥ የልብ ጥቅም ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ኦክስጅንና ምግብን ለህብረ ህዋሳት ማድረስ ሐ. ደም መርጨት

ለ. ለማዉራትና ለማሽተት መ. ካርቦን ዳይኦክሳይድና ቆሻሻን ከሰዉነታችን ማስወገድ

___17. ከሚከተሉት የአየር ምንዝሮች ዉስጥ 99 በመቶ የሚሸፍኑት የጋዝ አይነቶች እነማን ናቸዉ?

ሀ. ናይትሮጅን እና ካርበን ዳይኦክሳይድ ለ. ናይትሮጅን እና ሚቴን

ሐ. ኦክስጅን እና ናይትሮጅን መ. ኦክስጅን እና አርገን

___18. የኬክሮስ መስመሮች መነሻ ቦታ ምን ይባላል?

ሀ. የምድር ወገብ ለ. ሰሜን ሐ. ፕራይም ሜሪዲያን መ. ግሪንዊቺ

___19. የቋሚ መስመሮች አጠቃላይ ብዛታቸዉ ስንት ነዉ?

ሀ. 180 ለ. 90 ሐ. 360 መ. 120

---20. ከሚከተሉት ዉስጥ ኢትዮጲያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀጠና የቱ ነዉ?

ሀ. ሰሜናዊ አፍሪካ ለ. መካከለኛዉ አፍሪካ

ሐ. ምዕራባዊ አፍሪካ መ. ምስራቃዊ አፍሪካ

----21. ስለምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ፍፁማዊ መገኛዉ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከ 18°ሰሜን እስከ 27° ደቡብ ኬንትሮስ ይገኛል።

ለ. ፍፁማዊ መገኛዉ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከ 22°ምስራቅ እስከ 51°28’ምስራቅ ኬንትሮስ ይገኛል።

ሐ. ፍፁማዊ መገኛዉ በአፍሪካ ካርታ ላይ ከ 18°ደቡብ እስከ 27° ሰሜን ኬክሮስ ይገኛል።

መ. በአፍሪካ አህጉር መካከለኛዉ ክልል ይገኛል።

------22. የአንድን ሀገር መገኛ በልዩ ልዩ አቅጣጫ ከሚያዋስኑ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የምንጠቀምበት ዘዴ የቱ ነዉ?

ሀ. ኬንትሮስ ለ.ፍፁማዊ መገኛ ሐ. ኬክሮስ መ. አንፃራዊ መገኛ

------23. ከሚከተሉት ዉስጥ አንፃራዊ መገኛ የማይገለፅበት የቱ ነዉ?

ሀ. ደቡብ ለ. በዲግሪ ሐ. ምዕራብ መ. ሰሜን

------24. ከሚከተሉት ዉስጥ አግድም መስመሮችን የሚገልፃዉ የቱ ነዉ?

ሀ. መሬትን በሰሜናዊና በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ይከፍላሉ።

ለ. መሬትን በምስራቅና በምዕራብ እኩል ይከፍላል።

ሐ. መነሻቸዉ ግሪንዊች ሜሪዲያን ነዉ።

መ. ከሰሜን ወደ ደቡብ የተሰመሩ የሐሳብ መስመሮች ናቸዉ።

------25. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከሚታዩ ዐብይ ትይዩ መስመሮች በትክክል ከዲግሪዉ ጋር የተጣመረዉ የቱ ነዉ?

ሀ. የካንሳር መስመር - $23^{1/2^{\circ}}$ደቡብ ሐ. የምድር ወገብ - 90°

ለ. የካፕሪኮርን መስመር - $23^{1/2^{\circ}}$ደቡብ መ. የአርክቲክ ክበብ - $66^{1/2^{\circ}}$ደቡብ

-------26. አግድም መስመሮች ከቋሚ መስመሮች በምን ይለያሉ?


ሀ. ከሰሜን ወደ ደቡብ የተሰመሩ የሐሳብ መስመሮች ናቸዉ።

ለ. መሬትን በሰሜናዊና በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ይከፍላሉ።

ሐ. በአጠቃላይ 360 ናቸዉ።

መ. መነሻቸዉ ግሪንዊች ሜሪዲያን ነዉ።

ከተራ ቁጥር 27 – 31 ያለዉን ጥያቄ ከታች ያለዉን ምስል በመመልከት መልሱ።



-----27. በሰሜን ንፍቀ ክበብ የሚገኙ ቦታዎች(ነጥቦች) ስንት ናቸዉ?

ሀ. 3 ለ. 1 ሐ. 2 መ. 4

------28. 20° ሰሜን ኬክሮስ እና 20° ምስራቅ ኬንትሮስ የሚያሳየዉ ፊደል የቱ ነዉ?

ሀ. "ለ" ለ. "ሐ" ሐ. "መ" መ. "ሀ"

------29. ፊደል "ሐ" የሚያመለክተዉ ቦታ ፍፁማዊ መገኛ በዲግሪ ከተቀመጠዉ ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. 20° ሰሜን ኬክሮስ እና 10° ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ. 30° ደቡብ ኬክሮስ እና 10° ምዕራብ ኬንትሮስ

ሐ. 0° ኬክሮስ እና 0° ኬንትሮስ

መ. 40° ሰሜን ኬክሮስ እና 30° ምስራቅ ኬንትሮስ

-----30. ፊደል "ሀ" የሚያመለክተዉ ቦታ ፍፁማዊ መገኛ በዲግሪ ከተቀመጠዉ ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. 20° ሰሜን ኬክሮስ እና 10° ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ. 20° ደቡብ ኬክሮስ እና 40° ምዕራብ ኬንትሮስ

ሐ. 0° ኬክሮስ እና 0° ኬንትሮስ

መ. 40° ሰሜን ኬክሮስ እና 30° ምስራቅ ኬንትሮስ

-----31. ስለ 0° ኬክሮስ እና 0° ኬንትሮስ ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በምድር ወገብ እና በግሪንዊች ሜሪዲያን ላይ መሆኑን ያሳያል።

ለ. የአግድምና የቋሚ መስመሮችን ማዕዘናዊ ርቀት ያሳያል።

ሐ. ፍፁማዊ መገኛን ይገልፃል።

መ. አንፃራዊ መገኛን ይገልፃል።

------32. ከሚከተሉት ዉስጥ የምስራቅ አፍሪካ መገኛ ጥቅም የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በትልልቅ ዉሃማ አካላት መከበባቸዉ በቀላሉ በቅኝ ገዥዎች እንዲወረሩ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ለ. በምጣኔ ሀብት ዕድገት እንዳያሳድጉ ያደርጋቸዋል።

ሐ.ባላቸዉ የወደብ አገልግሎት ጠንካራ የንግድ ትስስር እንዲኖራቸዉ ያደርጋል።

መ.የባህር በር የሌላቸዉ ለከፍተኛ የየብስ ትራንስፖርት ወጪ ይዳረጋሉ።

-----33. ከሚከተሉት ዉስጥ የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገር የሆነችዉ ሀገር የቷ ናት?

ሀ. ሪዩኒየን ለ. ሩዋንዳ ሐ. ኬንያ መ. ስዊዚላንድ

------34. የህንድ ዉቅያኖስ ደሴት ያልሆነችዉ ሀገር የቷ ናት?

ሀ. ሲሸየልስ ለ. ቡሩንዲ ሐ. ኮሞሮስ መ. ሞሪሽየስ

-------35. የታላላቅ ሐይቆች ክልል የሆነችዉ ሀገር የቷ ናት?

ሀ. ሶማሊያ ለ. ጂቡቲ ሐ. ሩዋንዳ መ. ማዳጋስካር

------36. ከሚከተሉት ዉስጥ የአፍሪካ ቀንድ ሀገር ያልሆነችዉ ሀገር የቷ ናት?

ሀ.ታንዛኒያ ለ.ጂቡቲ ሐ. ሶማሊያ መ.ኤርትራ

------37. የአፍሪካ ትልቁ ደሴት ማን ይባላል?

ሀ.ሞሪሽየስ ለ. ሪዩኒየን ሐ.ኮሞሮስ መ. ማዳጋስካር

------38. ከአፍሪካ ረጅሙ ወንዝ የቱ ነዉ?

ሀ. ዛምቤዚ ለ. ገናሌ ሐ. ናይል መ. ሩቩማ

--------39. የኢትዮጲያ ትልቁ ሀይቅ የቱ ነዉ?

ሀ. ሀዋሳ ሐይቅ ለ. ዝዋይ ሐይቅ ሐ. ላንጋኖ ሐይቅ መ. ጫሞ ሐይቅ

--------40. በኢትዮጲያ ዉስጥ የሚገኛዉ ስምጥ ሸለቆ ከየት እስከ የት ነዉ?

ሀ. ከአፋር - ደቡብ ለ. ከኦሮሚያ - አፋር

ሐ. ከእስያ - ሞዛምቢክ መ. ከእስያ - ኢትዮጲያ

--------41. በሁለት የመሬት መሰንጠቅ መካከል ያለዉ ቦታ ወደ ላይ ሲነሳ የተፈጠረ ተራራ የቱ ነዉ?

ሀ. ሜሩ ለ. ሩዋንዞሪ ሐ. ኪሊማንጃሮ መ. ራስ ደሽን

--------42. የኢትዮጲያ ትልቁ ተራራ የቱ ነዉ?

ሀ. ሩዋንዞሪ ለ. ኤልጎን ሐ. ኪሊማንጃሮ መ. ራስ ዳሽን

--------43. የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በአፍሪካ ብቻ ምን ያህል ኪሎሜትር ርዝመት አለዉ?

ሀ. 5600 ኪ.ሜ ለ. 6500 ኪ.ሜ ሐ. 7200 ኪ.ሜ መ. 2700 ኪ.ሜ

--------44. በኢትዮጲያ ዉስጥ የማይገኘዉ የስምጥ ሸለቆ ሐይቅ የቱ ነዉ ?

ሀ. ዝዋይ ሐይቅ ለ. የሻላ ሐይቅ ሐ. ኪቩ ሐይቅ መ. አባያ ሐይቅ

--------45. የመሬትን ትክክለኛ ምስል ለማየት የሚያስችል መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ.ጂፒኤስ ለ. ጎግል ኧርዝ ሐ.ጎግል ማፕ መ.ጎግል ካርታ

--------46. ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየትና ለመመርመር የሚያገለግለዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ጎግል ካርታ ለ. ኮምፓስ ሐ.ጂፒኤስ መ. ጎግል ማፕ

--------47. የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ዉስጥ የምትጠቃለለዉ ሀገር የቷ ናት?

ሀ. ናይጄሪያ ለ. ዩጋንዳ ሐ. ቻድ መ. ቶጎ

--------48. የኢትዮጲያ ፍፁማዊ መገኛ ልኬት የቱ ነዉ?

ሀ. 12°- 18° ሰ ኬክሮስና 36°- 44° ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ. 3°ሰ - 4° ደ ኬክሮስና 33°- 41° ምስራቅ ኬንትሮስ

ሐ. 3°-15° ሰ ኬክሮስና 33° - 48° ምስራቅ ኬንትሮስ

መ. 33°-48° ሰ ኬክሮስና 3°- 15° ምስራቅ ኬንትሮስ

--------49. ምስራቅ አፍሪካን ከሚያዋስኑ ዉሃማ አካላት መካከል ትልቁ ማን ይባላል?

ሀ. የህንድ ዉቅያኖስ ለ. የኤደን ባህረ - ሰላጤ

ሐ.የአትላንቲክ ዉቅያኖስ መ. የፓስፊክ ዉቅያኖስ

--------50. ኦክስጅንና አልሚ ምግቦች ለሰዉነታችን የሚሰራጩበትና ካርቦንዳይ ኦክሳይድ እና ሌሎች ቆሻሻዎች በደም አማካኝነት የሚሄዱበት ሂደት ምን ይባላል?

ሀ. ደም ለ. የደም ህዋስ ሐ. የደም ዑደት መ. የደም ስሮች

--------51. ከሚከተሉት አንዱ የደም ህዋስ አይደለም።

ሀ. ቀይ የደም ህዋስ ለ. ደም - መልስ ሐ. ነጭ የደም ህዋስ መ. ፕላትሌት

--------52. ከሚከተሉት ስለ ቀይ የደም ህዋስ ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በሽታ ለመከላከል ሐ. ደም ለማርጋት

ለ. አየር ለማስተላለፍ መ. ጀርሞች ወደ ሰዉነታችን ሲገቡ ለማጥቃት

--------53. ከሚከተሉት ስለደም ህዋሶች ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ቀይ የደም ህዋስ- ኦክስጅንን ከሳንባ ተቀብለዉ በመሸከም ለመላ የሰዉነታችን ህዋሶች ያደርሳሉ።

ለ. ነጭ የደም ህዋስ- የበሽታ አምጪ ተህዋሲያንን ወደሰዉነታችን ሲገቡ ለማጥቃት ያገለግላል።

ሐ. ፕላትሌት - ሰዉነታችን ሲደማ ብዙ ደም እንዳይፈስ ለማርጋት ይጠቅማል።

መ. ቀይ የደም ህዋስ - በቁጥራቸዉ ከቀይ የደም ህዋሶች ይበልጣሉ።

--------54. የደም ስሮች ተግባር ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ደምን ከልብ ወደ ተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ማሰራጨት

ለ. ደምን ከሰዉነታችን ወደ ልብ መመለስ

ሐ. በሽታን ለመከላከል

መ. ደምን በሰዉነታችን ዉስጥ ማዳዝ

--------55. ደምን ከተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ወደ ልብ የሚያደርሰዉ የደም ስር ዓይነት የቱ ነዉ?

ሀ. ደም-ቅዳ ለ. ደም - መልስ ሐ. ፕላትሌት መ. ቀጫጭን የደም ስሮች

---------56. ለሰዉነታችን ህዋሶች በጣም ቅርብ የሆነዉ የደም ስር የቱ ነዉ?

ሀ. ደም- ቅዳ ለ. ቀጫጭን የደም ስሮች ሐ. ደም -መልስ መ. ፕላትሌት

----------57. የልብ ትርታን የምናዳምጥበት መሳሪያ ምን ይባላል?

ሀ. ቴሌስኮፕ ለ. ማይክሮስኮፕ ሐ. ስቴቶስኮፕ መ. ፔሬስኮፕ

----------58. ከሳንባ በኦክስጂን የበለፀገ ደም በፑልሞናሪ ቬይን ተቀብሎ ወደ ግራ አቀባይ ልበ-ገንዳ የሚልካዉ የልብ ክፍል የቱ ነዉ?

ሀ. ቀኝ ተቀባይ - ልበ ገንዳ ሐ. ግራ ተቀባይ ልበ-ገንዳ

ለ. ግራ ተቀባይ - ልበ ገንዳ መ. ግራ አቀባይ - ልበ ገንዳ

-------59. ደም ኦክስጂንን የሚቀበለዉ ከየትኛዉ የሰዉነት ክፍላችን ነዉ?

ሀ. ሳንባ ለ. ልብ ሐ. ኩላሊት መ. ጉበት

--------60. ከሚከተሉት የልብ ክፍሎች ተግባር በትክክል ቅደም ተከተሉን የጠበቀዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ግራ አቀባይ ልበ-ገንዳ → ቀኝ አቀባይ ልበ-ገንዳ → ቀኝ ተቀባይ ልበ- ገንዳ → ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ለ. ቀኝ አቀባይ ልበ-ገንዳ → ግራ አቀባይ ልበ-ገንዳ → ቀኝ ተቀባይ ልበ- ገንዳ → ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ሐ. ቀኝ ተቀባይ ልበ-ገንዳ → ቀኝ አቀባይ ልበ-ገንዳ → ግራ ተቀባይ ልበ- ገንዳ → ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

መ. ግራ ተቀባይ ልበ-ገንዳ → ቀኝ ተቀባይ ልበ-ገንዳ → ግራ አቀባይ ልበ- ገንዳ → ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ

--------61.በጉርምስና ወቅት በወንዶች ላይ የሚታየዉ ስነ- ህይወታዊ ለዉጥ የቱ ነዉ?

ሀ. የድምፅ መቅጠን ለ. የዘር ፈሳሽ ማመንጨት

ሐ. የዳሌ መስፋት መ. የወር አበባ መታየት

----------62. በሁለቱም ፆታዎች ላይ የማይታዉ ስነ-ህይወታዊ የቱ ነዉ?

ሀ. ፈጣን የሆነ የክብደት መጨመር ሐ. ፈጣን የሆነ የቁመት መጨመር

ለ. በብብትና በብልት አካባቢ ፀጉር ማብቀል መ. የትካሻና የደረት መስፋት

----------63. ከሚከተሉት ስለወር አበባ ትክክል ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ሴቶች አላስፈላጊ የሆኑ የደም ቆሻሻዎችን የሚያስወግዱበት ተፈጥሮአዊ ክስተት ነዉ።

ለ. በማህፀንና በእንቁልጢ ዉስጥ የሚካሄድ ወርሃዊ ዑደት ነዉ።

ሐ. ኮረዳዋ ልጅ መውለድ የማትችልበት የዕድሜ ክልል ነዉ።

መ. ከ 12 – 55 ዓመት ዕድሜ ክልል ዉስጥ በሴቶች ላይ የሚታይ ነዉ።

---------64. ሰዎች ለግል ፍላጎታቸዉ በሎሎች ሰዎች ላይ ዖታን መሰረት ያደረገ ትንኮሳና አስገድዶ መድፈር ----------ይባላል።

ሀ. እንጥል መቧጣጥ ለ. ዉርጃ ሐ. ዖታዊ ጥቃት መ. ጋብቻ

----------65. አየርን ወደ ሰዉነታችን ዉስጥ የምናስገባበት ሂደት ምን ይባላል?

ሀ. ኢ- ምጋት ለ. ምጋት ሐ. ካርቦንዳይኦክሳይድ መ. ኦክስጅን

--------66. አየር ወደ ዉስጥ ስንተነፍስ አየር ወደ ሳንባችን ለመድረስ የሚያልፍበቸዉ አካላት ቅደም ተከተል ሲቀመጡ፡-

ሀ. የአፍንጫ ቀዳዳ → ሰርን → ድህረ-አፍ → አብይ ትንቧ → ተገንጣይ ትንቧ → ደቂቅ ትንቧ → ትንከረት

ለ. ትንከረት → ደቂቅ ትንቧ → ተገንጣይ ትንቧ → አብይ ትንቧ → ድህረ-አፍ → ሰርን → የአፍንጫ ቀዳዳ

ሐ. ድህረ-አፍ → ሰርን → ተገንጣይ ትንቧ → አብይ ትንቧ → ደቂቅ ትንቧ → ትንከረት → የአፍንጫ ቀዳዳ

መ. ሰርን → ድህረ-አፍ → አብይ ትንቧ → ደቂቅ ትንቧ → ትንከረት → ተገንጣይ ትንቧ → የአፍንጫ ቀዳዳ

-------67. ለኦክስጅንና ለካርቦንዳይኦክሳይድ ወደ ደም ዉስጥ መግቢያና መዉጫ ሆኖ የሚያገለግለዉ የመተንፈሻ አካል የቱ ነዉ?

ሀ. አብይ ትንቧ ለ. ድህረ - አፍ ሐ. ትንከረት መ. ደቂቅ ትንቧ

-------68. ከሚከተሉት ዉስጥ የመተንፈሻ አካሉ እና ተግባሩ የማይገናኘዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ሰርን - አየር ያሞቃል፣ቆሻሻንና ጀርምን ያጣራል።

ለ. ደቂቅ ትንቧ - አየር ወደ አየር ትንከረት መግቢያና መዉጫ ሆኖ ያገለግላል።

ሐ. ድህረ - አፍ -የአየር መግቢያና መዉጫ ነዉ።

መ. ተገንጣይ የአየር ቧንቧ - ከዐብይ ትንቧ ወደ ሳንባ ለሚገባዉና ለሚወጣዉ መዉጫ ሆኖ ያገለግላል።

-------69. የስርዓተ ትንፈሳ ጠቀሜታ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ለማዉራትና ለማሽተት ሐ. ኦክስጂንን ለህዋሶቻችን ማሰራጫት

ለ. የልብ ትርታን መለካት መ. ሙቀትና ቅዝቃዜን ለማመጣጠን

-------70. ከሚከተሉት ዉስጥ ስለ ስርዓተ ትንፈሳ ሂደት ትክክል የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በአፍንጫ ከመተንፈስ ይልቅ በአፍ መተንፈስ ይመረጣል።

ለ. ድልሺ ወደታች ሲወርድ የደረት ወና ስለሚጠብ የአየር ግፊት ይጨምራል።

ሐ. ድልሺ ወደታች ሲወርድ የደረት ወና ስለሚሰፋ የአየር ግፊት ይቀንሳል።

መ. ድልሺ ወደቦታዉ ሲመለስ የአየር ግፊት ይቀንሳል።

--------71. ከሚከተሉት ዉስጥ የምጋትና ኢ-ምጋት የአየር ምንዝሮች በመቶኛ በትክክል ያልተቀመጠዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ናይትሮጂን- 21%፣ 16% ሐ. ናይትሮጂን - 78%፣ 78%

ለ. ካርቦንዳይኦክሳይድ - 0.03% ፣ 4% መ. ኦክስጂን - 21%፣ 16%

---------72. ከሚከተሉት ድብልቅን በትክክል የሚገልፀዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ልዩ ቁሶች ኬሚካዊ በሆነ መንገድ መጣመር

ለ. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ልዩ ቁሶች አካላዊ በሆነ መንገድ መጣመር

ሐ. ከመቀላቀላቸዉ በፊትና በኋላ ያላቸዉን ማንነትና ባህሪ መቀየራቸዉ

መ. ኬሚካዊ በሆነ መንገድ ስለተጣማሩ ምንዝሮቹ ባህሪያቸዉን ይለዉጣሉ።

--------73. ከሚከተሉት ዉስጥ የዋህድ - ዘር ባህሪ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. በድብልቁ ዉስጥ ያሉትን ምንዝሮች በአይን ወይም በአጉሊ መነፅር መለየት አይቻልም።

ለ. በድብልቁ ዉስጥ ያሉትን ምንዝሮች በአይን ወይም በአጉሊ መነፅር መለየት ይቻላል።

ሐ. በአብዛኛዉ ዋህድ - ዘር ድብልቆች ሙሙት ናቸዉ።

መ. የድብልቁ ይዘት ወጥና ተመሳሳይ ነዉ።

---------74. ከሚከተሉት ዉስጥ ድብልቅ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ወተት ለ. ውሃ ሐ. ደም መ. አየር

---------75. ከሚከተሉት ዉስጥ ልይ - ዘር ድብልቅ የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ወተት ለ. የዘይትና ዉሃ ድብልቅ ሐ. ደም መ. አየር

--------76. በድብልቅ ዉስጥ የሚገኝ ፈሳሽ ምንዝርን በዝግታ በማንቆርቆር ከሌላኛዉ ካልሚሙ ጠጣሮች ወይም ፈሳሾች የምንለይበት ዘዴ የቱ ነዉ?

ሀ. ቀረራ ለ. ንጥረት ሐ. ጥሊያ መ. ትነት

----------77. በቀላሉ ሊተካ ወይም ሊታደስ የማይችል የጉልበት ምንጭ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. የፀሐይ ብርሃን ለ. ንፋስ ሐ. የድንጋይ ከሰል መ. ዉሃ

----------78. አንድን ነገር ለሁለት ለመክፈል የሚረዳ የቀላል መኪና ክፍል የቱ ነዉ?

ሀ. ሽብልቅ ለ. መፈንቅል ሐ. ሽክርክሪት መ. መፍቻ

----------79. ከሚከተሉት ዉስጥ የቀላል መኪና መሳሪያ ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. የመኪና ማንሻ ለ. አካፋ ሐ. ፒንሳ መ. መቀስ

80. ምሥራቅ አፍሪካ ከአጠቃላይ የአፍሪካ መልከዓ ምድር ይዘት ---------- በመቶ ይሸፈናል።

ሀ/ 15 ሐ/ 4 0

ለ/ 21 መ/ 3 0

81. ከሚከተሉት የምሥራቅ አፍሪካ ተራሮች ውስጥ በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ያልተፈጠረው የቱ ነው?

ሀ/ ኪሊማንጃሮ ተራራ ሐ/ ሜሩ ተራራ

ለ/ ራስ ደጀን ተራራ መ/ የሩዋንዘሪ ተራራ

82. ስለ አግድም ወይም ትይዩ መስመሮች ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ መነሻቸው በዜሮ ዲግሪ ላይ ነው

ለ/ በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የተሠመሩ ናቸው

ሐ/ መነሻቸው ግሪንዊች ሜሪዲያን ይባላል

መ/ በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ የተሠመሩ ናቸው

83. የአካባቢ ታዋቂ ቦታዎችን ስም እና ዐራቱን መሠረታዊ አቅጣላዎችን በመጠቀም የምንገልፀው የመገኛ ዓይነት

ሀ/ አንፃራዊ መገኛ ሐ/ አካባቢያዊ መገኛ

ለ/ ፍፁማዊ መገኛ መ/ ግምታዊ መገኛ

84. የካንሰር መስመር የሚገኘው በስንት ዲግሪ ላይ ነው?

ሀ/ 23 ½ ሰሜን ሐ/ 66 ½ ሰሜን

ለ/ 23 ½ ደቡብ መ/ 66 ½ ደቡብ

85. የራስ ዳሽን ተራራ የከፍታ መጠን ስንት ነው?

ሀ/ 462 0 ኪሎ ሜትር ሐ/ 642 0 ሜትር

ለ/ 462 0 ሜትር መ/ 5,2 00ኪሎ ሜትር

86. መሬትን በሰሜን እና በደቡብ ንፍቀ ክበብ በእኩለ ቦታ ይከፍላል።

ሀ/ ቋሚ መስመሮች ሐ/ ግሪንዊች ሜሪዲያን

ለ/ ትልቁ ሜሪዲያን መ/ የምድር ወገብ

87. ከሚከተሉት የምሥራቅ አፍሪካ ተራሮች ውስጥ በትክክል ያልተጣመረው የቱ ነው?

ሀ/ ራስ ዳሽን ⟶ኢትዮጵያ ሐ/ ኤልጎን⟶ ዩጋንዳ

ለ/ ኪሊማንዳሮ ⟶ ኬንያ መ/ ሜሩ ተራሪ ⟶ ታንዛኒያ

88. የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ አጠቃላይ ርዝመቱ ስንት ኪሎ ሜትር ነው?

ሀ/ 56 ዐዐ ሐ/ 6500

ለ/ 27 ዐዐ መ/ 72 ዐዐ

89. በሕዋ ላይ በተቀመጡ እና በመሬት ዙሪያ በሚሽከረከሩ ሰው ሠራሽ ሳተላይቶች አማካኝነት የመሬትን ትክክለኛ ገፅታን ለማሳየት የሚያገለግል መተግበሪያ የቱ ነው?

ሀ/ ጂፒኤስ ለ/ ጎግል ኧርዝ ሐ/ ጎግል ካርታ መ/ የቦታና አቅጣጫ ማሳያ

90. የምሥራቅ አፍሪካን በስተ ምሥራቅ በኩል የሚያዋስነው ውሃማ አካል ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ/ የሕንድ ውቅያኖስ ሐ/ የፓስፊክ ውቅያኖስ


ለ/ የአትላንቲክ ውቅያኖስ መ/ ቀይ ባሕር

91. ከሚከተሉት ውስጥ ዓብይ የአግዳሚ መስመር ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ ግሪንዊች ሜሪዲያን ሐ/ የካፕሪኮርን መስመር

ለ/ የምድር ወገብ መ/ የካንሰር መስመር

ከተራ ቁጥር ***92- 94*** ያሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች ያለውን ምስል መሠረት በማድረግ መልሱ።



92. የፊደል ″ሀ″ ን ፍፁማዊ መገኛ የሚገልፀው ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ/ 1 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 2 ዐ⁰ ምሥራቅ ኬንትሮስ ሐ/ 3 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 1 ዐ⁰ ምሥራቅ ኬንትሮስ

ለ/ 2 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 2 ዐ⁰ ምዕራብ ኬንትሮስ መ/ 1 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 1 ዐ⁰ ምሥራቅ ኬንትሮስ

93. የፊደል ″ለ″ ን ፍፁማዊ መገኛ የሚገልፀው ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ/ 2 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 2 ዐ⁰ ምዕራብ ኬንትሮስ ሐ/ 2 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 2 ዐ⁰ ምሥራቅ ኬንትሮስ

ለ/ 3 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 3 ዐ⁰ ምሥራቅ ኬንትሮስ መ/ 1 ዐ⁰ ሰሜን ኬክሮስ እና 2 ዐ⁰ ምዕራብ ኬንትሮስ

94. በምስሉ ላይ ከተመለከቱት ፊደላቶች ውስጥ ለምድር ወገብ ይበልጥ ቅርብ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ ፊደል ″መ″ ሐ/ ፊደል ″ለ″

ለ/ ፊደል ″ሀ″ መ/ ፊደል ″ሠ″

95. ከሚከተሉት ውስጥ ከአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች የማይመደበው የትኛው ነው?

ሀ/ ኢትዮጵያ ለ/ ዩጋንዳ ሐ/ ኤርትራ መ/ ጅቡቲ

96. ምሥራቅ አፍሪካን የሚያዋስኑ ውሃማ አካላት መካከል ትልቁ

ሀ/ የኤደን ባሕረ- ሰላጤ ሐ/ የፓስፊክ ውቅያኖስ

ለ/ ቀይ ባሕር መ/ የሕንድ ውቅያኖስ

97. የአባይ ወንዝ መነሻ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገር ማን ትባላለች?

ሀ/ ኤርትራ ለ/ ኬንያ ሐ/ ኢትዮጵያ መ/ ጅቡቲ 98. በአፍሪካ ትልቁ ሐይቅ ተብሎ የሚታወቀው የቱ ነው?

ሀ/ ጣና ለ/ ማላዊ ሐ/ ቪክቶሪያ መ/ ታንጋኒካ

99. ልባችን ስንት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት?

ሀ/ 2 ሐ/ 5

ለ/ 6 መ/ 4

100. ፈሳሽ ከሆነ ፕላዝማ እና ከደም ሕዋሶች የተሠራ የአካላችን ክፍል ነው።

ሀ/ የደም ሥር ሐ/ የደም ዑደት

ለ/ ፕላዝማ መ/ ደም

101. ደምን ከልብ ወደ ተለያዩ ክፍሎች የሚያሰራጨው የደም ሥር የትኛው ነው?

ሀ/ ደም ቅዳ ሐ/ ቀጫጭን የደም ሥሮች

ለ/ ደም መልስ መ/ መልሱ አልተሰጠም

102. የልብ ትርታን የምናዳምጥበት መሣሪያ ምን ይባላል?

ሀ/ ኢንዶስኮፕ ሐ/ ቴሌስኮፕ

ለ/ ስቴቶስኮፕ መ/ አልትራሳውንድ

103. የነጭ የደም ሕዋሶች ተግባር የሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ በሽታ አምጭ ጀርሞችን ወደ ሰውነታችን ሲገቡ ማጥቃትና መከላከል

ለ/ ሰውነታችን ሲዳማ ብዙ ደም እንዳይፈስ ያረጋል

ሐ/ ኦክስጅንን ለመላ የሰውነታች ሕዋሶች ያደርሳሉ

መ/ በያዙት የሄሞግሎቢን ሃመልማል ኦክስጅንን ይሸከማል

104. ከቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ የተቀበለውን ደም በፑልሞናሪ አርተሪ ወደ ሳንባ የሚረጨው የልብ ክፍል

ሀ/ ቀኝ ተቀባይ ልበ ገንዳ ሐ/ ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ

ለ/ ቀኝ አቀባይ ልበ ገንዳ መ/ ግራ አቀባይ ልበ ገንዳ

105. አየርን ወደ ሰውነታችን የምናስገባበት ሂደት ምን ይባላል?

ሀ/ ትንፈሳ ሐ/ ኢምጋት

ለ/ ምጋት መ/ ትነት

106. በጉርምስና እና በኮረዳነት ወቅት በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚታየው ሥነ- ሕይወታዊ ለውጥ የሆነው የቱ ነው?

ሀ/ የድምፅ መጎርነን ሐ/ ፈጣን የክብደት እና የቁመት መጨመር

ለ/ የድምፅ መቅጠን መ/ በፊት ላይ ፀጉር መብቀል

107. የወር አበባ አማካኝ ወርሐዊ ዑደት በማህፀን እና በእንቁልጢ ውስጥ የሚካሄደው በየስንት ቀናት ነው?

ሀ/ 15 ሐ/ 18

ለ/ 2 0 መ/ 28

108. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የልብ ጥቅም አይደለም።

ሀ/ ደም መርጨት ሐ/ ካርቦን ዳይኦክሳይድን እና ቆሻሻን ከሰውነታችን ውስጥ ማስወገድ

ለ/ ኦክስጅን እና ምግብን ለሕብረ ሕዋሳት ማድረስ መ/ ካርቦን ዳይኦክሳይድን ለሕብረ- ሕዋሳት ማድረስ

1 0 9. የአየር መግቢያና መውጫ በመሆን የሚያገለግል የመተንፈሻ አካል ክፍል ነው።

ሀ/ የአፍንጫ ቀዳዳ ሐ/ ሰርን

ለ/ ትንከረት መ/ ደቂቃ ትንቧ

110. በሞጋት እና በኢምጋት ጊዜ ተመሳሳይ መጠን ያለው የአየር ምንዝር ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ/ ኦክስጅን ለ/ ካርቦን ዳይኦክሳይድ ሐ/ ናይትሮጅን መ/ የውሃ ትነት

111. ሁል ጊዜ ያለማቋረጥ በሥራ ላይ የሚገኘው የሰውነታችን ክፍል የቱ ነው?

ሀ/ ሳንባ ለ/ ልብ ሐ/ ልብ መ/ ዐይን

112. ከስምጥ ሸለቆ ውጭ ባሉ የምሥራቅ አፍሪካ ሐይቆች ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው?

ሀ/ ጣና ለ/ ታንጋኒካ ሐ/ ማላዊ መ/ ኪቩ

113. የማሳይ ማራ ፓርክ የት ሀገር ይገኛል?

ሀ/ ኬንያ ለ/ ኢትዮጵያ ሐ/ ዩጋንዳ መ/ ታንዛኒያ

114. የምሥራቅ አፈሪካን ፍፁማዊ መገኛ የሚገልፀው

ሀ/ ከ 18^0 ሰሜን እስከ 27^0 ደቡብ ኬክሮስ ሐ/ ከ 22^0 ምዕራብ እስከ 51^0 ምዕራብ ኬንትሮስ

ለ/ ከ 3^0 - 15^0 ሰሜን እና ከ 33^0 - 48^0 ምሥራቅ ኬክሮስ መ/ ከ 15^0 ሰሜን እስከ 22^0 ደቡብ ኬክሮስ

115. የቋሚ መስመሮች ምሥራቃዊ ብዛት ስንት ነው?

ሀ/ 36 ፀ ለ/ 18 ፀ ሐ/ 9 ፀ መ/ 6 ፀ

116. የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት በቀላሉ በቅኝ ገዥዎች እንዲወረሩ አስተዋፅኦ ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ/ ኢኮኖሚያቸው ዝቅተኛ መሆኑ ሐ/ በትልልቅ ውሃማ አካላት በመከበባቸው

ለ/ የተማረ የሰው ኃይል እጦት መ/ የንግድ ትስስ አለመኖር

117. የምሥራቅ አፍሪካ ከአምስቱ የአፍሪካ ቀጠናዎች በስፋት በስንተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል?

ሀ/ 5 ኛ ለ/ 3 ኛ ሐ/ 4 ኛ መ/ 2 ኛ

118. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የተሠመሩ የሐሳብ መስመሮች ምን ይባላሉ?

ሀ/ ኬክሮስ ለ/ ኬንትሮስ ሐ/ ቋሚ መስመሮች መ/ተቋራጭ መስመሮች

119. ወደ ሳንባችን የሚገባውን አየር በማሞቅ ቆሻሻንና ጀርሞችን የሚያጣራው የስርዓተ ትንፈሳ አካል ክፍል የቱ ነው?

ሀ. ትንባ ለ. ዲልሽ ሐ. ትንከረት መ. ሰርን

120. ዶታን ጥቃት ምንድን ነው?

ሀ. ዶታን መሠረት ያደረገ የትምህርት ስርዓት

ለ. ዶታዊ አድሎ ማካሄድ

ሐ. ያለዕድሜ የሚፈጠር የስራ ጫና

መ. ዶታን መሠረት ያደረገ ትንኮሳና አስገድዶ መድር

121. የኦክስጅንና የካርበንዳይኦክሳይድ ልውውጥ የሚደረገው በየትኛው የስርዓተ ትንፈሳ ክፍል ነው?

ሀ. ትንከረት ለ. ድህረ አፍ ሐ. ሰርን መ. ባላ ትንባ

122. የታላላቅ ሀይቆች ክልል የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ኢትዮጵያና ጅቡቲ ሐ. ኤርትራና ሶማያ

ለ. ኬንያና ዩጋንዳ መ. ኢትዮጵያና ሶማሊያ


123. የካንሰር መስመር የሚገኘው በየትኛው ንፍቀ ክበብ ነው?

ሀ. ደቡብ ለ. ሰሜን ሐ. ምዕራብ መ. ምስራቅ

124. ኢትዮጵያ በየትኛው የአፍሪካ ክልል ትገኛለች?

ሀ. በማዕከላዊ ለ. በምስራቃዊ ሐ. በደቡባዊ መ. በሰሜናዊ

ከተራ ቁጥር 7-11 ያሉትን ጥያቄዎች አግዳሚና ቋሚ መስመሮችን በመጠቀም መልሱ።



125. ለምድር ወገብ ቅርብ የሆኑት ፊደሎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መ እና ሐ ለ. ሐ እና ሠ ሐ. ሀ እና ሠ መ. ሀ እና መ

126. የፊደል ሀ ፍፁማዊ መገኛን የሚያሳየው የትኛው ነው?

ሀ. 20^0 ሰሜን ኬክሮስ 20^0 ምዕራብ ኬንትሮስ

ለ. 10^0 ደቡብ ኬክሮስ - 20^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

ሐ. 10^0 ሰሜን ኬክሮስ - 10^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

መ. 20^0 ሰሜን ኬክሮስ -30^0 ምዕራብ ኬንትሮስ

127. 20^0 ደቡብ ኬክሮስ እስከ 20^0 ምዕራብ ኬንትሮስ የሚገኘው ፊደል የቱ ነው?

ሀ. ፊደል ሠ ለ. ፊደል መ ሐ. ፊደል ሐ መ. ፊደል ሀ

128. ደቡብ ንፍቀ ክበብ ላይ የሚገኙት ፊደሎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መ እና ሀ ለ. ሠ እና መ ሐ. ሠ እና ሐ መ. ሐ እና ሀ

129. ሰሜን ንፍቀ ክበብ ላይ የሚገኙት ፊደሎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ፊደል መ እና ሐ ሐ. ፊደል ሀ እና መ

ለ. ፊደል ሀ እና ሠ መ. ፊደል ሐ እና ሠ

130. የቪክቶሪያ ሀይቅን የሚያዋስኑት ሀገራት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ኬንያ፣ታንዛኒያና ዩጋንዳ ሐ. ሞዛምቢክ፣ማላዊና ታንዛኒያ

ለ. ሩዋንዳ፣ብሩንዲና ማላዊ መ. ታንዛኒያ፣ዛምቢያና ብሩውንዲ

131. ከትንሽ ወደ ትልቅ ባላቸው ከፍታ መሰረት የተቀመጡት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ኪሊማንጃሮ ⟶ ኬንያ ተራራ ⟶ ሩዋንዛሪ

ለ. ሩዋንዛሪ ⟶ የኬንያ ተራራ ⟶ ኪሊማንጃሮ

ሐ. ራስ ዳሽን ⟶ ኤልጎን ⟶ ኪሊማንጃሮ

መ. ኪሊማንጃሮ ⟶ ሩዋንዛሪ ⟶ የኬንያ ተራራ

132. የምስራቅ አፍሪካ አጎራባች ሀገሮች ስንት ናቸው?

ሀ. ሰባት ለ. ስምንት ሐ. አምስት መ. አስራ ስምንት

133. የልብ ተግባር ምንድን ነው?

ሀ. ደምን መፍጠር ሐ. የደም ህዋስ መፍጠር

ለ. ደምን መርጨት መ. ደምን ማርጋት

134. መሬትን በሉል ወይም በካርታ ላይ ምስራቅና ምዕራብ ንፍቀ ክበብ ብለው የሚከፍሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ቋሚ መስመሮች ሐ. የኬክሮስ መስመሮች

ለ. አግዳሚ መስመሮች መ. ትይዩ መስመሮች

135. የአንታርክቲካ መስመር ስንት ዲግሪ ላይ ይገኛል?

ሀ. 60 $1/2^0$ ሰሜን ለ.66 $½^0$ ደቡብ ሐ. 23 $1/2^0$ መ. 23 $½^0$ ደቡብ

136. የኢትዮጵያ ፍፁማዊ መገኛን የሚገልፀው የቱ ነው?

ሀ. ከ 15^0 ሰሜን እስከ 33^0 ምስራቅ

ለ. ከ 3^0 – 15^0 ሰሜን ኬክሮስ እና ከ 33^0-48^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

ሐ. ከ 48^0 – 54^0 ሰሜን ኬክሮስ እና 43^0 – 48^0 ምስራቅ ኬንትሮስ

መ. ከ 15^0-3^0 ምስራቅ ኬንትሮስ እና 33^0 – 48^0 ሰሜን ኬንትሮስ

137. በዩጋንዳ የሚገኘው ተራራ የትኛው ነው?

ሀ. ራስ ዳሽን ለ. ኤልጎን ሐ. ሩዋንዛዊ መ. ሜሩ

138. የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ አጠቃላይ ርዝመቱ ስንት ነው?

ሀ. 5600 ኪ.ሜ ለ. 7200 ኪ.ሜ ሐ. 6500 ኪ.ሜ መ. 6200 ኪ.ሜ

139. መሀላቸው ላይ ጎድጎድ ያሉና የዶናት ቅርፅ ያላቸው የደም ህዋሳት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ቀይ የደም ህዋሳት ሐ. እንክብሊቶች

ለ. ነጭ የደም ህዋሳት መ. ፕላትሌት

140. ደም ሲፈስ በፍጥነት እንዲቆም ማድግ የየትኛው የደም ክፍል ተግባር ነው?

ሀ. ፕላዝማ ለ. ቀይ የደም ህዋስ ሐ. ነጭ የደም ህዋስ መ. ፕላትሌት

141. የደም ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከበሽታ ለመከላከል ሐ. የምግብ ልመትን ማፍጠን

ለ. አየር ለማስተላለፍ መ. ደምን እንዲረጋ ማድረግ

142. በሰውነታችን ውስጥ ስንት የደም ቧንቧዎች አሉ?

ሀ. ሁለት ለ. ሶስት ሐ. አራት መ. አምስት

143. ለሰውነታችን ህዋሳት በጣም ቅርብ የሆኑ የደም ቧንቧዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ደም ቅዳ ሐ. ቀጫጭን የደም ስሮች

ለ. ደም መልስ መ. ትልቁ ደም ቅዳ

144. በላይ በኩል የሚገኙት የልብ ገንዳዎች ጥምረት የያዘው የቱ ነው?

ሀ. ግራ ተቀባይና ግራ አቀባይ ሐ. ቀኝ አቀባይና ግራ አቀባይ

ለ. ቀኝ ተቀባይና ግራ ተቀባይ መ. ግራ አቀባይና ቀኝ ተቀባይ

145. ከግራ ሰጭ ልብ-ገንዳ ወደ ግራ ተቀባይ ልብ-ገንዳ ደም ወደኋላ እንዳይመለስ የሚያግደው ክፍክድ ምን ይባላል?

ሀ. ሶስተኛ ክፍክድ ለ. ሁለተኛ ክፍክድ ሐ. ደጋኔ ክፍክድ መ. አራተኛ ክፍክድ

146. ደም ወሳጅ ቧንቧ ሆኖ ያልተጣራ ደም ከልብ ወደ ሳንባ የሚወስድ የደም ቧንቧ የቱ ነው?

ሀ. ሳንባዊ ደም መልስ ሐ. ትልቁ ደም መልስ

ለ. ሳንባዊ ደም ቅዳ መ. ትልቁ ደም ቅዳ

147. ደምን ከሰውነት ወደ ልብ የሚያጓጉዘው የደም ስሮች ምን ይባላሉ?

ሀ. ርቂቶች ለ. ደም መላሽ ሐ. ደም ቅዳ መ. ደም ወሳጅ

148. በኦክስጂን የበለፀገ ደምን ከሳንባ ተቀብሎ ወደግራ ተቀባይ ልብ ገንዳ የሚያጓጉዘው የቱ ነው?

ሀ. ትልቁ ደም መልስ ሐ. ሳንባዊ ደም መልስ

ለ. ትልቁ ደም ቅዳ መ. ሳንባዊ ደም ቅዳ

149. ወፍራም ግድግዳ ያለው የልብ ገንዳ የትኛው ነው?

ሀ. ቀኝ ተቀባይ ልብ ገንዳ ሐ. ግራ አቀባይ ልብ ገንዳ

ለ. ግራ ተቀባይ ልብ ገንዳ መ. ትልቁ ደም መልስ

150. በኦክስጂን ያልበለፀገ ደምን የሚያጓጉዘው የልብ ገንዳዎችን ጥምረት የያዘው የትኛው ነው?

ሀ. ቀኝ ተቀባይና ግራ ተቀባይ ሐ. ቀኝ ተቀባይና ቀኝ አቀባይ

ለ. ግራ አቀባይና ግራ ተቀባይ መ. ግራ አቀባይና ቀኝ አቀባይ

151. ለተሽከርካሪና በበራሪ አካላት አቅጣጫ ለመጠቆምና ፍጥነት ለመቆጣጠር የሚያግዘው መሣሪያ

ሀ. ጎግል ካርታ ለ. ጎግል ማፕ ሐ. ጂፒ ኤስ መ. ካርታ

152. በጉርምስና ወቅት በወንዶች ላይ የሚታይ ስነ-ህይወታዊ ለውጥ የትኛው ነው?

ሀ. የጡት ማደግ ለ. የዳሌ መስፋት ሐ. የጡንቻ መዳበር መ. የድምፅ መሰለል

153. የወር አበባ ዑደት በአማካኝ ስንት ቀናትን ጠብቆ ይመጣል?

ሀ. በ 15 ቀናት ለ. 10 ቀናት ሐ. 20 ቀናት መ. 28 ቀናት

154. ደምን ከሰውነት ተቀብሎ ወደ ቀኝ ተቀባይ ልብ ገንዳ የሚረጨው ምን ይባላል?

ሀ. ግራ አቀባይ ልብ ገንዳ ሐ. ትልቁ ደም ቅዳ

ለ. ትልቁ ደም መልስ መ. ግራ አቀባይ

155. በኦክስጂን ያልበለፀገ የደም ዑደትን የሚያሳየው የትኛው ነው?

ሀ. ሰውነት →ትልቁ ደም መልስ ቀኝ ተቀባይ ቀኝ አቀባይ ሳንባዊ ደም ቅዳ ሳንባ →

ለ. ሳንባ →ሳንባዊ ደም መልስ ግራ ተቀባይ ግራ አቀባይ ትልቁ ደም ቅዳ ሰውነት→

ሐ. ሰውነት →ትልቁ ደም ቅዳ ሳንባዊ ደም መልስ ትልቁ ደም መልስ ቀኝ ተቀባይ ቀኝ አቀባይ

መ. ሳንባ →ትልቁ ደም መልስ ቀኝ ተቀባይ ቀኝ አቀባይ ግራ አቀባይ ትልቁ ደም ቅዳ

156. ስለ ነጭ የደም ህዋሳት ትክክል የሆነው የቱ ነው

ሀ. በሽታን ይከላከላል ሐ. ሂሞግሎቢን አላቸው

ለ. ክብ ቅርፅ አላቸው መ. ደም እንዲፈስ ያደርጋሉ

157. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ወንዝ የቱ ነው

ሀ. ሩቩማ ለ. ዛምቢዚ ሐ. ታና መ. ገናሌ

158. ፈሳሹ የደም ክፍል ምን ይባላል

ሀ. ፕላዝማ ለ. የደም ህዋስ ሐ. ነጭ የደም ህዋስ መ. ርቂቶች